


ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም

# የሚዞር ነገር ተመልሶ ይመጣል

እንደመለስ ዜናዊ ከአንድ ጎሣ በመወለዱ የሚኩራራ ሰው፤ እኔ ከዚህ ጎሣ በመወለዴ እኮራለሁ የሚል ሰው ምን ማለቱ ነው? እስቲ በጥሞና እስቡት፤ አንድ ሰው እኔ ከአንድ እገሌ ከሚባል መናጢ ደሀ በመወለዴ እኮራለሁ፤ እኔ ከአንድ እገሌ ከሚባል ደጃዝማች በመወለዴ እኮራለሁ፤ …ወዘተ. ማለት በእውነት ምን ማለት ነው? መኩራትስ ምን ማለት ነው? ሁለት ዓይኖች ስላሉኝ እኮራለሁ! አምስት ጣቶች ስላሉኝ እኮራለሁ! መኩራት በአግባቡ የሚቻለው በሠሩት መልካም ሥራ ነው፤ በአጋጣሚ የሚሆን ነገር ሁሉ የሚያኮራ ከሆነ ምንም የማያኮራ ነገር የለም፤ እንኳን ከማንም ተራ ሰው ይቅርና ከአንድ ንጉሠ ነገሥትም ቢወለድ የሚያኮራ ነገር የለም።

አንድ ሰው መኩራት የሚችለው እሱ ራሱ አስቦና ተንቀሳቅሶ ባስገኘው ውጤት ነው፤ ያውም ቢሆን ልዩና ፊር ቀዳጅ ሲሆን ነው፤ ውሀ ከቧንቧ የቀዳ ሁሉ እኮራለሁ ካለ ኩራት ጥንቡን ጣለ ማለት ነው፤ ጥንቡን የጣለ ኩራት ባዶ ግም ነው፤ በሆን-ባልሆን ምክንያት በአጋጣሚ የተገኘ ነገር ሁሉ አያኮራም፤ ለምሳሌ ከአንድ ሰካራም መወለድ ያሳፍራል እንጂ አያኮራም፤ ሳር የማይበቅልበት በረሀ ውስጥ መወለድ ያስጨንቃል እንጂ አያኮራም፤ በአሜሪካ ወይም በአውሮፓ ነጭ ሆኖ መወለድ አያኮራም፤ በአውሮፓም ሆነ በአሜሪካ ነጭነት በጥቂት ጥቁሮች ላይ የበላይነትን ሊያጎናጽፍ በመቻሉ ይመች ይሆናል፤ ግን ተመርጦ አልተገኘምና አያኮራም፤ ዱሮ ዱሮ በድንጋይ ዳቦ ዘመን አንዱ የግሪክ ተወላጅ ግሪክ እንጂ አረመኔ ባለመሆኔ፣ ነጻ ሰው እንጂ ባርያ ባለመሆኔ፣ ወንድ እንጂ ሴት ባለመሆኔ እኮራለሁ ብሎ ነበር፤ ጥራዝ-ነጠቅ ሁሉ ይህንን ተውሶ እኮራለሁ ቢል የሚገልጸው ባዶነቱን ብቻ ነው።


በትግራይ በመወለዱ ብቻ እያንዳንዱ ትግሬ ተመችቶታል የሚል አስተሳሰብ ከወያኔ ጎሠኛነት የተጸነሰ ውላጅ ነው፤ ብዙ ሰዎች ከወያኔ ዘረኛነት በንዴት ተነሥተው ትግሬ ሁሉ በወያኔ አገዛዝ ተመችቶታል ወደሚል መደምደሚያ ይደርሳሉ፤ በተለይም ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ አብዛኛዎቹ ትግሬዎች ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር በአደባባይ ቆመው ወያኔን ባለመቃወማቸው የወያኔ ደጋፊዎች በመሆናቸው ነው ወደሚል ማጠናከሪያ ተደረሰ፤ መነሻው ወያኔዎች ሁሉ ትግሬዎች ናቸው፤ በትግራይ የሚኖሩ ሁሉ ትግሬዎች ናቸው፤ ስለዚህ ወያኔዎችና ትግሬዎች አንድ ናቸው፤ ስለዚህ ወያኔ በሥልጣን ላይ ሆኖ ትግሬዎችን ሁሉ ወይም አብዛኛዎቹን አደላድሎአቸዋል፤ ማለት አንካሳ ወይም ቆማጣ አስተሳሰብ ነው፤ ላዩን ሲያዩት የወያኔን ጎሠኛነት ለመቃወም የተፈተለ ይመስላል፤ ነገር ግን ሌላም ዓላማ አለው፤ ሌላ ጎሠኛነትን ያራምዳል፤ ስለዚህም በመነሻውም ሆነ በመድረሻው ከሕገ ኀልዮት ጋር ይጋጫል፤

አንደኛ በትግራይ ክልል ውስጥ የሚኖሩት ትግሬዎች ብቻ አይደሉም፤ ትግሬ ያልሆኑ ሌሎችም አሉ፤

ሁለተኛ በትግራይ ውስጥ በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ደሀዎች፣ በችጋር የሚሰቃዩ ምስኪኖች፣ አዲስ አበባ ድረስ ልጆቻቸውን ይዘው የሚመጡ ችግረኞች አሉ፤ እነዚህን ቆጥረን አንዘልቃቸውም፤ ይህ የማይካድና የታወቀ እውነት ነው፤

ሦስተኛ በአንጻሩ ደግሞ በትግራይ፣ በአዲስ አበባ፣ ምናልባትም በዱባይ፣ በአውሮፓና በአሜሪካ ግንበ ሰናኦርን የሚገነቡ በመቶዎች የሚቆጠሩ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በያሉበት የዓለም ክፍሎች ገንዘብ ያከማቹና የሚያከማቹ የትግራይ ተወላጆች አሉ፤ እነዚህ በሥልጣንና በሀብት ላይ ተቃቅፈው ድብን ያለ እንቅልፍ ወስዶአቸው፤ እንኳን የደሀዎቹን የትግራይ ሰዎች ጩኸትና የልጆቻቸውን ችግር የመረዳት ብቃት የላቸውም፤ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ደሀ መከራና ስቃይ ወደ ጆሮአቸውና ወደ ዓይናቸው አይደርስም፤ ከሲአይኤ (የአሜሪካ የስለላ ድርጅት) በቀር የሚሰሙት የለም፤ በሰብአዊ መብቶች ድርጅቶች ሁሉ በየጊዜው የሚሰማው የዓለም ሁሉ ጩኸት ለነሱ ጆሮ ባዕድ ነው፤ ይህም ጸሐይ የሞቀው እውነት ነው፤ መካድ አይቻልም።

አራተኛ በሚልዮን በሚቆጠሩት ሙልጭ ያሉ የትግራይ ደሀዎችና በመቶ በሚቆጠሩት መሬት በጠበበቻቸው የትግራይ ቱጃሮች መሀከል በሺሆች የሚቆጠሩ የትግራይ ተወላጆች ይኖራሉ፤ እነዚህ ኑሮአቸውን ለማሸነፍ ሲሉ በመቶዎች ለሚቆጠሩት የትግራይ ቱጃሮች በሎሌነት ያደሩና የታዘዙትን ሁሉ የሚፈጽሙ የግል ነጻነትም ሆነ የግል ሀሳብ የሌላቸው ወይም ማሰብ ያልተፈቀደላቸው መሣሪያዎች ናቸው፤ የታሰበለትንና የተነገረውን በትግርኛም ሆነ በአማርኛ፣ ወይም በእንግሊዘኛ አፉ እንዳመጣ ሳያመነታ የሚናገር መለስ ዜናዊ ብቻ ነበር፤ ማሰብ ለወያኔ እንግዳ ነገር ነው፤ አሁን በቅርቡ በዋሽንግተን የስብሐት ነጋ ጠባቂዎች ያደረጉት ጉልህ ማስረጃ ነው።




በመጀመሪያው የወያኔዎችን ቁጥር፣ ሁለተኛ የሎሌዎቻቸውን ቁጥር በግምትም ቢሆን ለማወቅ እንሞክር፤ የእኔ ሙከራ እንደሚከተለው ይሆናል፤ ስዕሉን ብንመለከተው ወያኔ የምለው የሀ) ማለት፣ የወያኔ መሪዎችና ሹማምንት፣ የለ) ማለት፣ የወያኔ ሎሌዎችና አገልጋዮች ድምርን ነው፤ በሀ)ና በለ) ያሉት ቁጥሮች ላይ እንዴት ተደረሰ? ለመነሻ ያደረግሁት የወያኔ ሹማምንትን ቁጥር ነው፤ እነሱን 15,000 (አሥራ አምስት ሺህ) አደርግኋቸው፤ ከዚያ የበለጡ ቢሆኑ የአገሩ ሀብት አይበቃቸውምና የማያባራ ቅራኔና ግጭት ውስጥ ይገቡ ነበር ብዬ ገመትሁ፤ ግን እነዚህ ሹማምንት ዘመዶቻቸውንና የግል አገልጋዮቻቸውን ጨምሮ አንድ ሚልዮን አምስት መቶ ሺህ ያህል (1,500,000) ይሆናሉ ብለን እናስብ፤ የወያኔ ድርጅት ሎሌዎች ደግሞ 150,000 ቢሆኑና እያንዳንዳቸው አምስት የግል አሽከርና ዘመድ ቢኖራቸው፣ ቁጥራቸው ወደ 750,000 ይደርሳል፤ የወያኔ ሎሌዎች ከትግራይ ብቻ እንዳልሆኑ ሳንጠራጠር ተቀብለን በዚህ የሎሌዎች ቁጥር ውስጥ ከትግራይ ውጭ የገቡ ሰዎች መኖራቸውን አብረን እንድንረዳው ያሻል፤ ይነሱና ይብዙ እንጂ ከሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች ሎሌዎች ሞልተዋል፤ በዚህ ምክንያት የወያኔ አገልጋዮች የትግራይ ተወላጆች ብቻ አይደሉም ለማለት እንችላለን፤ በአገልጋዮቹ ውስጥ

ወደ ገፅ 35 ዞሯል

# የሚዞር ነገር . . .

ከ ገፅ 6 የዞረ

ባለው ተዋረድ የትግራይ ተወላጆች የበላይነት ቢኖራቸውም፣ ሌሎች ዱላና ገመድ አቀባዮችና ጠመንጃ ተሸካሚዎች አሽከሮች መኖራቸውን መካድ አይቻልም፣ ሁላችንም አይተናል!

የትግራይ ህዝብ ቁጥር 6,065,000 (ከስድስት ሚልዮን አንድ መቶ ሺህ ትንሽ አነስ ያለ) ነው ብንል፣ የወያኔን ሹማምንትና ሎሌዎች ስናነሣ 3,799,500 (ሦስት ሚልዮን ሰባት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺህ አምስት መቶ) ግድም ይቀራል፤ እነዚህ ደሀ ትግሬዎች ናቸው፤ እነዚህ የወያኔ ፍርፋሪም ያልደረሳቸው ሙልጭ ያሉ ደሀዎች ናቸው፤

የጉሣ ጥራት ከታሰበ በሁለተኛው ምድብ ውስጥ፣ ማለትም ሥልጣንና ሀብት በተቃቀፉበት ውስጥ መሆን አለበት፤ ወያኔ ለሥልጣንም ይሁን ለሀብት ቀናተኛ ሆኖ ከሌላ ጉሣ አላስገባም ቢል ይህንን መረዳት አስቸጋሪ አይሆንም፤ ታምራት ላይኔንና ሌሎችንም በውርደት ሲያራግፉ አይተናል፤ ሥልጣን በሌለበት ሁሉ ከሌሎች ጉሣዎች ሰዎች መደልደል ይቻላል፤ ሥልጣን ከነሠይፉ ባለበት ወንበር ላይ ግን ከወያኔ ሌላ አይቀመጥበትም፤ (ወያኔ ከትግራይ መሆኑ ትግራይን ወያኔ አያደርገውም፤) የፕሬዚዳንቱ ወንበር ሥልጣን ሲያገኝ መለስ ወንበሩን ለወጠ፤ ኢያስበው እግዚአብሔር ወንበሩን አነሣበትና ሰው የሰባል፣ እግዚአብሔር ይፈጽማል የሚባለው ነገር ደረሰ፤ መለስ ምክትል አድርጎት የነበረው ኃይለማርያም ደሳለኝ ጠቅላይ ሚኒስትር ተባለ፤ ወያኔ ተረበሸ፤ ኃይለማርያምን ማስወገዱ ብቻ ሳይሆን ኃይለማርያምን መተካቱም እያዳለጠ የሚጥል መንገድ ሆነ፤ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሮች ዙሪያውን አጥረው ወጥረው ሥልጣኑን በረዙት፤ ስለዚህ ለወያኔ የመለስ ሥልጣን ወደወል የወያኔ ሥልጣን የተለወጠ ይመስላል።

ማንም ሰው ቢሆን ለሚኖረው ኑሮ አብዛኛው ኃላፊነት የራሱ ነው፤ በሁለተኛው ምድብ ውስጥ የጠቃለልኋቸው በሥልጣን ሠፈር ያሉት ትግሬዎችም ለኑሮአቸው ኃላፊነትን መቀበል አለባቸው ማለት ነው፤ የእነዚህ በሥልጣን ሠፈር ያሉ ትግሬዎች ኑሮ በጣም የተለየ ነው፤ ሰው ሁሉ በላይ ናቸው፤ ችግርን ይፈጥራሉ እንጂ እነሱ ችግር የለባቸውም፤ ለኑሮአቸውም ኃላፊነቱ የራሳቸው ነው፤ እንኳን ለራሳቸው ኑሮና ለቀረውም የኢትዮጵያ ሕዝብ ኑሮ ኃላፊነት አለባቸው፤ በአንደኛው ምድብ ውስጥ ያሉትን ደትግራይ ካልሄድን እዚሁ አዲስ አበባ ስልመና መጡ ብቻ የምናያቸው ናቸው፤ በተቀር አዲስ አበባ የሚርመሰመሱት ሁሉ የሁለተኛውና የሦስተኛው ምድቦች ናቸው።

በሦስተኛው ምድብ ውስጥ ያሉትን ትግሬዎች ወያኔ ከመጣበት የኢትዮጵያ ክፍል መምጣታቸውና ትግርኛ በመናገራቸው ብቻ ከግንብ ሰናኦር ባለቤቶች ጋር በኑሮ ማዛመድ ነገር ያለበት አስተሳሰብ ነው፤ ቀደም ሲል የደተጠቀሰው ኃላፊነትና ተጠያቂነት ከሰዎች ጋር የተያያዙ በመሆናቸው ለዕለት ...ሳቸው አዲስ አበባ ድረስ መጥተው ...ሊለምኑ ሰዎችን ኑሮ ከግንብ ሰናኦሩ ባለቤቶች ... ጋር ለማያያዝ የተፈጥሮ ዝምድና መፈለግ ...ፍና ጉልህ የሆነውን ልዩነት ችላ ማለት ነው፤ በሁለቱ ኑሮዎች መሀከል ያለውን ልዩነት ችላ ማለት ነው፤ እንዲያውም የጎሣ አስተሳሰብን ማራመድ ነው።

ፈረንጆች ሲተርቱ የሚዞር ነገር ሁሉ ወደተነሣበት ይመለሳል፤ ይላሉ። □